# የስደት መንግሥት የችግራችን መፍትሔ ይሆናል ወይስ መንስኤ?

ይሄንን "የስደት መንግሥት" የሚባልን ነገር እንደሰሞኑ ሁሉ ከሦስት ዓመታት በፊትም በጨረፍታ አሰምተውን ነበር፡፡ እኔ አሁን በዚህ ጽሑፍ የዚህን ጉዳይ ክወናውን (ቴክኒካል የሆኑ ነገሮችን) ለማተት ወይም ይሄንን ጉዳይ እያስኬዱት ስላሉ ሰዎች ብዙ የማውቀው ነገር ኖሮኝ ከእነሱ ሰብእና አኳያ ይሄንን ሐሳብ ለመፈተሽም አይደለም፡፡ ነገር ግን ከነባራዊ ሁኔናዎች ተነሥቶ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ መባል የሚገባው ብዙ ነገር አለና እሱን ማለት ነው የፈለኩት፡፡

መጀመሪያ "የስደት መንግሥት" የሚለውን ነገር እንደሰማሁ በተጨባጭ ያሉ ነባራዊ ሐቆችን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ሐሳብ ከመሆኑና በባዶ ምኞት ብቻ የተንጠለጠለ ከመሆኑ የተነሣ ግርምት የተሞላ ሳቅ ነበር ያጫረብኝ፡፡ ብልጣብልጥ የሆኑ የመሰላቸው ሰዎች ያሰቡት የትም የማያደርስ አስቂኝ ድራማ (ትውንተ ኩነት) ሆኖ ነበር የታየኝ፡፡

እንደሚመስለኝ እነዚህ ወገኖች ይሄንን ሐሳብ ለማሰብ ያበቃቸው ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን አገዛዝ መጥላቱ፣ በቃኝ ማለቱ፣ ከዳር እስከዳር በወያኔ የተንገሸገሸና ወያኔን መገላገል የሚፈልግ መሆኑ ነው፡፡ ያለው ሁኔታ እንዲህ መሆኑም "በድንገት ሕዝባዊ ዐመፅ ተቀስቅሶ ወያኔ ይወገዳል፣ ይወድቃል፣ ይከላል" የሚል እምነት ማሳደራቸው ነው "ተዘጋጅተን እንጠብቅ" ብለው ለማሰብ ያበቃቸው፡፡ እኔ በግኔ ሰዎቹ ይህን በማሰባቸው ያላቸውን አስተዛዛቢ የብስለትና የማገናዘብ ጠልቆ የማሰብ ደረጃ፣ ለሀገራችን ፖለቲካ የቱን ያህል ሩቅ እንደሆኑ እንድገነዘብ አድርጎኛል፡፡

እነዚህ ወገኖቻችን ያልተደኑቸው ነገሮች ምን ምን መሰሏቹህ?፦ እውነት ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ በቅቶታል፣ በወያኔ ተንገሽግሿል፣ እጅግ ተማሯል እንዲህም ከሆነ ብዙ ቆይቷል አሁን አይደለም እንዲህ የሆነው፡፡ አሁን ጥያቄው "የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ ከበቃው፣ በወያኔ ከተንገሸገሸና ፍጹም ተስፋ ከቆረጠ የቆየ ከሆነ በሕዝባዊ ዐመፅ ለመገላገል ያልሞከረው ለምንድን ነው ታዲያ?" የሚለው ነው፡፡

እነኝህ የስደት መንግሥት አቋቋምን የሚሉ ወገኖቻችን ይሄንን ጥያቄ ለማጤንና ለመመለስ ሙከራ ቢያደርጉ ኖሮ እኔ እርግጠኛ ነኝ በእንዲህ ዓይነቱ ቅዠት አያስቡትም ነበር፡፡

እነሱ ያሰቡት "በቃ! ሕዝቡ ተማሯል ከተማረረ ደግሞ ማመፁ አይቀርም፤ ዐምፆ ወያኔ በተወገደ ጊዜ ክፍተት ተፈጥሮ ሀገራችን ችግር ላይ እንዳትወድቅ" በሚል አጋጣሚውን ተጠቅመው ሥልጣን ለመያዝ ከመፈለግም ሊሆን ይችላል ብቻ

ከሁለቱ በዘንዱ ምክንያት ተዘጋጅተን እንጠብቅ የሚለውን ብቻ ነው ያሰቡት፡፡ ሰዎቹ በሰጡት መግለጫ የገለጹት "ወያኔ በድንገተኛ ዐመፅ ሲወገድ ክፍተት ተፈጥሮ ሀገሪቱና ሕዝቧ ችግር ላይ እንዳይወድቁ ተዘጋጅቶ ለመጠበቅ!" የሚል ነው፡፡

ነገሮችን አገናዝቦ መመልከት ለሚችል ሰው ግን ይሄ ሽፋን እንጅ ሰዎቹ የሚሉትን ያህል ለሀገርና ለወገን ተቆርቋሪ ሆነው የሀገርና የወገን ጉዳይ እረፍት ነስቷቸው ይሄንን እንዳላሰቡ የእያንዳንዳቸውን የኋላ ፖለቲካዊ (እምነተ አሥተዳደራዊ) እንቅስቃሴ ታሪካቸውን በዳሰሳቹህ ጊዜ ትረዱታላቹህ፡፡ በቀላሉ እነዚህ ተጠራርተው የተሿሿሙት ወገኖቻችን "የሀገርና የወገን ጉዳይ አስጨንቋቸው፣ እረፍት ነስቷቸው ስለሀገርና ስለወገን ሲሉ ሳይፈሩና ሳያፍሩ ተጋፋጭ ሆነው በየመድረኩ ወያኔን ሲሞግቱ፣ ሲያወግዙ፣ ሲቃወሙ፣ ሲገዳደሩ፣ ሲከሱ፣ ሲወቅሱ፣ ሲፈታተኑ ያሳለፏቸውና እያሳለፏቸው ያሏቸው የትግል ተሞክሮዎች አሏቸው ወይ?" ብላቹህ ስትጠይቁ በምታገኙት መልስ ይሄንን ያልኳቹህን ጉዳይ ልትታዘቡ ትችላላቹህ፡፡

ዋናው ጥያቄ እንዳሉት ወያኔ ቢገረሰስ ተከትሎት ሊመጣ ከሚችለው ተገማች ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ሀገራችን ችግር ላይ እንዳትወድቅ መረጋጋት እንዲፈጠር ማድረግ የሚችለው "የታጠቀ ኃይል ነው ወይስ የሆኑ ሰዎች ተቧድነው ሆነናል የሚሉት የስደት መንግሥት የተባለው**?"** የሚለው ነው፡፡

ለማንኛውም በየትኛው ምክንያት ተነሣሥተው እንዲህ ሊያስቡ እንደቻሉ ለጊዜና ለእግዚአብሔር እንተወውና ይህ ድርጊታቸው ግን የትም የማያደርስና ይልቁንም የሚጎዳ የማይጠቅም ስለ መሆኑ ዕንይ፡-

በነገራችን ላይ እጅግ በሚገርማቹህ ደረጃ ሲጀመር ጀምሮ "ዐመፅ ይነሣል፣ አይ! ዘንድሮማ ወያኔ ያበቃለታል!" ወዘተረፈ. ዓይነት ወሬዎችን ትንቢት እያስመሰለ ከየእምነት ቦታዎች እስከ የሥራ ቦታዎች ድረስ ሁሉም ቦታ ላይ የሚያስወራው ወያኔ እራሱ እንደሆነ ታውቃላቹህ? ለምንስ ይመስላቹሀል?

ይሄንን የሚያደርግበት ምክንያት ለምን መሰላቹህ! እኔ መቸም ለጥቅማቸው ሲሉ የወያኔን መኖር የሚፈልጉት መካሪዎቹ ነጫጭ ሰይጣኖች ምዕራባዊያኑ ይሆናሉ እንጅ ይሄንን መሰሪ አስተሳሰብ ወያኔ ጭንቅላት ኖሮት ያስበዋል ብየ ለማመን እጅግ እቸገራለሁ፡፡

ነገር ግን "ሰብአዊነት ስለሚገደን፣ ለሀገርና ወገን ማሰብና መቆርቆራችን፣ ግብረገብነታችን ስለሚይዘን፣ ክፋትና ሸር የዕኩያን ተግባር ነው ብለን ስለናቅነው ልናደርገው አንፈልግም እንጅ ሥራየ ብለን እናድርገው ብንል መልካም ነገር ማድረግ ነው እንጅ የሚያስቸግረው ክፋትና ሸር መሥራት ደሞ ምኑ ያቅታል? ለክፋትና ተንኮልማ ሰይጣኑን ራሱ አጋዥ አባሪ አይደለም ወይ?" ብላቹህ ካላጣጣላቹህት በስተቀር እኔ በጣም ይገርመኛል ይደንቀኛልም፡፡

ወያኔዎቹ እንደዚህ ዓይነት ወሬዎቹን ሥራዬ ብለው በሁሉም ቦታዎች የሚያስወሩበት ምክንያት "እንዲህ ሊደረግ ነው! እንዲህ ሊሆን ነው!" ተብሎ ለሕዝቡ ሲወራለት ሕዝቡ ይሆናል ይደረጋል ተብሎ የሚነገር ጉዳይ ባለቤት እራሱ መሆኑን ትቶ "ላምፅ፣ ተደራጅቶ ልታገል" ሳይል እጅና እግሩን አጣምሮ ይሄ "እንዲህ ሊሆን ነው! እንዲህ ሊደረግ ነው!" የተባለውን ነገር ብቻ በመጠባበቅ ዘመኑን የሚፈጅ ይሆናል፣ ሰው ሁሉ የሚሆነውን ለማየት ራሱን በተመልካች በታዛቢ ቦታ ላይ አስቀምጦ "ሊሆን ነው!፣ ሊደረግ ነው!" የተባለውን ለማየት ይጠባበቃል እንጂ "የራሴ ጉዳይ ባለቤቱ እኔው እራሴ ነኝ፣ ለእኔ ያለሁት እኔው እራሴ ነኝ፣ ለእኔ ብሎ ከሌላ ቦታ መጥቶ ስለእኔ ዋጋ ከፍሎ እኔን ነፃ ሊያወጣኝ የሚችል ኃይል የለም አይኖርምም ስለዚህ የራሴን ጉዳይ እኔው ራሴ ልጨርሰው ልከውነው" ብሎ ጉዳዩን የራሱ አድርጎ አይነሣም አይንቀሳቀስም፡፡

"ዐመፅ ይነሣል!፣ ዘንድሮ ወያኔ ያበቃለታል!" ተብሏል ማየት የሚፈልገው ያንን ዐመፅ እነማን አንሥተውት ወያኔ እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚወገድለት መመልከት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ዘዴ ወያኔ ሕዝቡ የራሱን ጉዳይ የራሱ አድርጎ እንዳያስብ፣ መፍትሔም እንዳያፈላልግና እራሱ ዋጋ ከፍሎ ነጻ እንዳይወጣ ጉዳዩን የሚጨርስለት የምናብ ሌላ ሦስተኛ አካል ፈጥሮ ትወናውን በማድረግ እድሜውን እስከ አሁን ማራዘም ችሏል፡፡ ሕዝቡ እስኪነቃበት ድረስም ወደፊትም ሲጠቀምበት እንደሚቆይ እገምታለሁ፡፡

ይሄንን የምለው ፈጥሬ ወይም እንዲሁ በግምት እንዳይመስላቹህ**!** መረጃ አለኝ፡፡ ከበፊት ጀምሮ "በመጪው ዓመት፣ በቀጣዩ ጊዜ እንዲህ ይሆናል! እንዲህ ይደረጋል! ዐመፅ ይነሣል!" ወዘተረፈ. እያሉ እያስወሩ ሕዝቡን ከሚያጃጅሉ ከሚያዘናጉ የወያኔ ሰዎች አንዱን ተከታትየ አጥንቸው ነበር፡፡

ይህ ሰው "ቅዱስ ነኝ" ይላል ደመና ጠቅሶ ሳይቀር ወደ ፈለገበት እንደሚሔድ ሁሉ ይናገራል፡፡ ወያኔዎች የጨነቀው መላ ያጣ ሕዝብ ምንም ቢባል ላጣራ ልመርምር ሳይል እንደሚያምን እንደሚጃጃል ገብቷቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ ደፍረው "ቅዱስ ነኝ በደመና ላይ ተጭኜ ወደፈለኩበት እጓዛለሁ" ምንትስ ሲሉ ጥቂትም እንኳን አይሸማቀቁም አይደነግጡም አይጨነቁም፡፡ ልክ እውነት እንደሚናገር ሰው በልበ ሙሉነት እንዲህ ዓይነቱን ቅጥፈት ማታለያ ማወናበጃ ቃል ይናገሩታል፡፡

እናም ይሄ "ቅዱስ ነኝ ድንግላዊ ነኝ" ምንትስ እያለ በየገዳሙ በየጸበሉ እየዞረ የሚያወናብድን ወያኔ ስከታተለው የእግዚአብሔርም ፈቃድ ሆኖ ተጋለጦ ሲለው ባልጠበኩት አጋጣሚ ባለትዳርና የልጆች አባት ሥራውም የወያኔ ደኅንነት (ሰላይ) መሆኑን ደረስኩበት፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብየ "ትንቢት" እያለ ይናገራቸው የነበሩትን ነገሮችና ነገረ ሥራውን ሁሉ ሳስብ በቀጥጣም ይሁን በተዘዋዋሪ ሆን ተብሎ ታስቦባቸው ወያኔን ተጠቃሚ ሊያደርጉ በሚያስችሉ መልኩ ሕዝቡን በሥነልቡና መስለብ ማደንዘዝ የሚያስችሉ ሆነው አገኘኋቸው፡፡

እንደዚህ ሰው ያሉ በርካታ ካድሬዎች በየ እምነት ተቋማቱና እንደ አስፈላጊነቱ በሁሉም ቦታ አሉ፡፡ ይህንን ሥራም ሲሠሩ አገዛዙ በመንግሥት ስም ከሚሠራቸው የሥራ ክንውኖችና አቅዶች ጋር በሚገባ በመቀናጀት በማሰላሰል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ ካንገሸገሸው ካቅለሸለሸው ከበቃው የቆየ ሆኖ እያለ ዐምፆ እንዳይገላገለው ካደረጉት ምክንያቶች አንደኛው ይህ ሲሆን ሌላኛውና ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ወያኔ እንደምታዩት የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀደም ሲል ነጻነቱንና መብቶቹን በመንፈግና መፈናፈኛ በማሳጣት፣ መብታቸውን ለማስከበር በሚሞክሩት ላይ ኢሰብአዊ የመቀጣጫ የቅጣት እርምጃ በመውሰድ፣ ሩቅ ካልሆኑ ዓመታት ወዲህ ደግሞ ከመንግሥት ሠራተኛ እስከ ግል ሠራተኛ፣ ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከተማሪ እስከ ሠራተኛ ፍጹም በቁጥጥሩ ስር አድርጎ ከእሱ አስተሳሰብ ውጭ ማድረግ አይደለም ማሰብም እንኳን እንዳይችል ለማድረግ ፍጹም ኢዲሞክራሲያዊ (ኢመስፍነ ሕዝባዊ) በሆነ አሠራር በግዳጅ በአንድ ለአምስት አደረጃጀት ጠርንፎ አማራጭ አስተሳሰቦችን እንዳያስተናግድ ተጠፍንጎ የተያዘበት የታሰረበት በር የተዘጋበት ሁኔታ ላይ ያለ በመሆኑ ሕዝቡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ስር ሆኖ ዐመፅ አድርጎ ይሄንን የተንገሸገሸውን የተጸየፈውን አገዛዝ ለመገላገል በፍጹም እንዳይችል አድርጎታል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ ካንገሸገሸው፣ ካቅለሸለሸው፣ ከበቃው የቆየ ሆኖ እያለ ዐምፆ እንዳይገላገለው ካደረጉት ምክንያቶች ሦስተኛውና ዋነኛው ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡-

በግልጽ እንደምታዩት ወያኔ የፋሽስት ጣሊያንን "ከፋፍለህ ግዛ" የአገዛዝ ዘዴን እንዳለች ወስዶ በመጠቀም ሕዝቡን በብሔረሰብ በሃይማኖት በጾታ ሳይቀር ከፋፍሎ እጅግ ኃላፊነት በጎደለውና ድንቁርና በተሞላበት መልኩ እርስ በእርሱ እንዲተላለቅ ሊያደርጉት የሚችሉ ሰይጣናዊ ሴራዎችን በመጠንሰስ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ እንዳይሆን፣ እንዳይተባበር፣ እንዲቂያቂያምና ተፈራርቶ በጎሪጥ እየተያየ እንዲኖር፣ ቀን እየተጠባበቀ እንዲኖር እንዳደረገው ይታወቃል፡፡

ወያኔ ይሄንንም ያደረገበት ምክንያት ሕዝቡ ሕዝባዊ ዐመፅን እንዳያስብ እንዳይሞክረው ለማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም እርስ በእርሱ የሚፈራራ በጎሪጥም እንዲተያይ የተደረገ ሕዝብ እየገዛው ያለው አንባገነናዊ አገዛዝ የቱንም ያህል አስከፊ፣ ፈላጭ ቆራጭ፣ አረመኔና ሊገላገለው የሚፈልግ ቢሆንም እንኳን እየመረረውም ቢሆን አርፎ ተሰብስቦ ይኖራል እንጅ ዐምፆ ለማስወገድ ሊሞክር አይደለም ሊያስብም አይፈልግም፡፡ በሆነ አጋጣሚ በአንድ አካባቢ ዐመፅ ቢቀሰቀስም እንኳ ሌላኛውም አካባቢ የዐመፁ ተካፋይ ተሳታፊ ተባባሪ አይሆንም፡፡ ይሄንንም ባለፈው ወያኔ ኦሮሚያ ብሎ በሚጠራው የሀገራችን ክፍል ከተሞች ዐመፅ በተቀሰቀሰ ጊዜ ተመልክታቹሀታል፡፡

የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐመፁን ያልተቀላቀለበት ምክንያት ደግሞ የዐመፁ ርእሰ ጉዳይ (አጀንዳ) የሆነው "የአዲስ አበባን ከተማ ለማስፋት የተያዘውን አቅድ መቃወም" የሚለው ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ለጎጠኝነት የቀረበ ስለሆነ፣ ይህ

ተቃውሞ እራስን ኢትዮጵያዊ አድርጎ ካለማሰብ የሚመነጭና የሀገሪቱ ዋና ከተማ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጅ የአንድ ብሔረሰብ ባለመሆኑ ከተማው የተፈለገውን ያህል ቢሰፋ ተቃውሞ ሊነሣበት የሚገባ ባለመሆኑ በአንዲት ሀገር ውስጥ ባለ ሕዝብ መሀል እንዲህ ያለ መከላከል ተገቢ እንዳልሆነ በመረዳቱ፣ ዐመፁን ያነሡ ሰዎች ከኢትዮጵያ ጥቅም ይልቅ ክልል ብለው የሚጠሩት ጥቅም ስለበለጠባቸውና ይህ አመለካከትም እጅግ ጠባብ አጥፊና የማይፈለግ በመሆኑ፣ አስፈላጊ አይደለም እንጅ እንተሳሰብማ ከተባለና በትክክለኛ መለኪያ የየብሔረሰቡ ቀየ፣ ርስት፣ ይዞታ፣ ሀገር ይከለል ቢባል "ክልላችን ነው አይነካብን!" ብለው ዐመፁን ያስነሡት የኦሮሞ ተወላጆች የኛ ነው የሚሉት ቦታ የእነሱ አለመሆኑ በሚገባ ስለሚታወቅ በእነኝህና በሌሎችም ምክንያቶች ብቻ ሳይሆን የተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐመፁን ያልተቀላቀለው ይልቁንም የተቀረው የሀገሪቱ ሕዝብም ዐመፁን ተቀላቅሎ ይሄንን አስከፊ አንባገነን አገዛዝ በዐመፅ ቢያስወግደው "አገዛዙ በጠነሰሰው ሰይጣናዊ ክፉ ሴራ የእርስ በእርስ መተላለቅ ሊከሰት ይችላል!" ብሎ እጅግ ስለሚፈራ ይህ እንዳይሆን ከመፈለጉ አንጻር አገዛዙ ክፉና አረመኔ የተጸየፈው ቢሆንም "በዐመፁ ወያኔን አስወግጀ ወደባሰ ችግር ውስጥ ከምገባ ቢመረኝም ሰጦ ለበጦ ብየ እየተገዛሁ በሰላም ብኖር ነው የሚሻለኝ!" ብሎ እንዲያስብ ስላደረገው ነው፡፡ እያየነው ያለው ይሄንኑ ነው፡፡ ነገም በሌላ ቦታ ተመሳሳይ ዐመፅ ቢቀሰቀስ ልናየው የምንችለው ተመሳሳዩን ነገር ነው፡፡

እናም የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔ ካንገሸገሸው ካቅለሸለሸው ከበቃው የቆየ ሆኖ እያለ ዐምፆ እንዳይገላገለው ካደረጉት ምክንያቶች ሌላኛውና ዋነኛው ምክንያት በዘር በሃይማኖት ተከፋፍሎ እንዲፈራራ፣ ቀን እንዲጠባበቅ፣ እንዲቂያቂያም በመደረጉ ነው፡፡ ለጊዜው እነዚህ ሦስት ምክንያቶች ይበቁናል፡፡

የብሔር ተኮር ፖለቲካን እያቀነቀኑ ያሉ የፖለቲካ (የእምነተ አሥተዳደር) ቡድኖች ደንበኛ የወያኔ ሰይጣናዊ ሴራ መጠቀሚያ ከመሆንና ለወያኔ ተጨማሪ ጉልበት አጋዥ ከመሆን ውጭ አእምሮ ልቡና ማስተዋል ኖሯቸው ይሄንን የወያኔን ሰይጣናዊ ሴራ በሚገባ ተረድተው ነቅተው ማርከሻውን ማክሸፊያውን መላ መንገድ ዘዴ ማመንጨት የሚችል ጭንቅላት የሌላቸው ሆኑ እንጅ መፍትሔው በጣም ቀላል ነበር፡፡

እሱም አንድነት ነው፡፡ አንድነት ቢፈጥሩ ወያኔ በሕዝቡ መሀል የዘራው የእርስ በእርስ ጥላቻ መፈራራትና መጠራጠር ሥጋት ይወገድና ሕዝቡ እንደ አንድ ልብ መካሪ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆኖ አንድ ሐሳብ አንድ ግንባር ፈጥሮ በዐመፅ ወያኔን የሚገላገልበትን ዕድል መጠቀም እንዲችል በማብቃት ወያኔ የቀበረውን ሰዓት ጠብቆ የሚፈነዳ ፈንጅ ማምከን ማክሸፍ ያቻል ነበር፡፡

ይህንን የአንድነት ስሜት በሕዝቡ ልብ መፍጠር እስካልተቻለ ጊዜ ድረስ በሕዝባዊ ዐመፅ ወያኔ ይወገዳል ብሎ ማሰብ እጅግ ጅልነትና አለማሰብ አለማስተዋል፣ ያሉ ነገሮችን መረዳት አለመቻል ነው፡፡ እንዴትስ ነው በመንገዱ ላይ ስንት ዓይነት ፈንጅ

ተቀብሮበት እያለ በዚያ መንገድ የተቀበረውን ፈንጅ የሚያውቀውን ሕዝብ ሒድበትና ነጻ ውጣ ልንል የምንችለው? አስቀድሞ ፈንጅውን ማምከንና መንገዱን ነጻ ማድረግ ግድ አይልም ወይ? አንድነትን ፈጥረን ያለበትን የእርስ በእርስ መፈራራት ካስወገድንለት ሕዝቡ መንገዱ ከፈንጅ ነጻ መሆኑን ያውቅና የማንንም ትዕዛዝ ሳይጠብቅ መሬት አንቀጥቅጥ ዐመፅ በማድረግ ወያኔን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቀብሮት ለመገላገል አንድ ቀንን እንኳን ማባከን የማይፈልግ ይሆናል፡፡

ይህ የወያኔ ፈንጅም ይመክንና መንገዱም ነጻ ይሆን ዘንድ የብሔር ተኮር የፖለቲካ (የእምነተ አሥተዳደር) ዘውግን በማቀንቀን የትጥቅ ትግልንም ሆነ ሰላማዊ ትግልን እያደረጉ ላሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች (የእምነተ አሥተዳደር ቡድኖች) ማስተላለፍ የምፈልገው ዐቢይ ጉዳይ ቢኖር፡- ኸረ እንዲያው እባካቹህ! ከዛሬ ነገ በስላቹህ ነገሮችን ትረዱና መፍትሔው ገብቷቹህ ወደ ትክክለኛውና ሁሉንም ተጠቃሚ ወደሚያደርገው አስተሳሰብ ትመጣላቹህ ብለን ስናስብ እናንተ ግን እጅግ በሚገርምና ግራ በሚያጋባ መልኩ አድሮ ጥሬ እየሆናቹህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻ የሚወጣበትን ብሩሕና መልካም ቀን የሚያይበትን ዘመን እጅግ እያራቃቹህት ትገኛላቹህ፡፡

ኸረ ተው! እባካቹህ! እያራመዳቹህት ያለው አስተሳሰብ ወያኔን ጠቅሞ እድሜውን እያራዘመው እንደሆነ እንዴት መገንዘብ ይሳናቹሀል? በዚህ የምትቀጥሉና ወያኔን በማገዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ልብ እንዳይሆን የምታደርጉ ከሆነ ወያኔ ዘለዓለማዊ ሆነ ማለት አይደለም ወይ? ወያኔ እናንተንም በመጠቀም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ አንድ እንዳይሆን፣ እርስ በእርሱ እንዲቂያቂያም፣ እንዲጠራጠር፣ ቀን እንዲጠባበቅ አድርጎት እንዳለ በሌላ በአንዳች አጋጣሚ ቢወድቅ ቢወገድ እንኳን እያራመዳቹህት ያላቹህት ዓላማ አቋም አስተሳሰብ ሕዝቡ እርስ በእርሱ ተላልቆ፣ ተጠፋፍቶ፣ ተፋጅቶ፣ እንዲያልቅ ያደርገዋል እንጅ እንዴት ሆኖ ነው ሰላምና መረጋጋት፣ ፍትሕና እኩልነት፣ ነጻነትና መብት ሊያገኝ ሊጎናጸፍ የሚያስችለው? ሰው እንዴት ዕድሜው እየገፋ ሲሔድ አይበስልም? እድሜ እኮ! ሰውን ይለውጣል ብዙ ያስተምራል አይደለም እንዴ? እንዴት ነው ታዲያ እናንተ ላይ ይሄ ሊሠራ ያልቻለው? እኔ እኮ ግራ ገባኝ!

ወደ ቀደመው ነገራችን ስንመለስ እነኝህን ሕዝባዊ ዐመፅ እንዳይነሣ እንዳይደረግና ወያኔ እንዳይወድቅ የሚገድቡ ነባራዊ ሁኔታዎችንና ተግዳሮቶችን "የስደት መንግሥት አቋቋምን" ያሉ ወገኖቻችን በፍጹም ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገቡ በየእምነት ተቋማቱና በተለያየ ቦታ ሆነው የወያኔ ካድሬዎች የሚያስወሩትን ወሬ ብቻ በማድመጥና በመታለል "ዐመፅ ይነሣል!" በሚል ተስፋ የስደት መንግሥት ያሉትን እስከማቋቋም ድረስ ተታለዋልና ተጃጅለዋልና ነው ከላይ "የብስለት ደረጃቸውን ታዘብኩት፣ ለሀገራችን ፖለቲካ (እምነተ አሥተዳደር) ሩቅ እንደሆኑ እንድገነዘብ አደረገኝ" ማለቴ፡፡

ይህ እንቅስቃሴያቸውም ማድረግ የሚገባንን ነገሮች በጊዜውና በሰዓቱ ቶሎ በመቀናጀት አድርገን ሀገራችንን ነጻ እንዳናወጣ ሌላ የመዘናጊያ ጊዜ እንድናሳልፍ ጊዜ ገንዘብ እውቀት እንድናባክን አንድነት ኅብረት እንዳይኖረንና እንድንከፋፈል አድርጎ የሚያዳክመን በመሆኑ እንቅስቃሴው በቶሎ መገታት ይኖርበታል ብየ አምናለሁ፡፡

በዚህ እንቅስቃሴ ያላቹህ ወገኖቻችን እውነት ወያኔ በዚህች ሀገርና ሕዝቧ ላይ የሚያዘንበው ግፍና መከራ አሳስቧቹህ ነጻ መውጣታችንን ከሆነ የምትፈልጉት ለዚህም የጸና አቋም ካላቹህና ቁርጠኞች ከሆናቹህ ያለን አማራጭና መንገዱ አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡ የአርበኞች ግንቦት አባትን የትጥቅ ትግል መቀላቀልና በጽናት በቁርጠኝነት መታገል፡፡

ይሄንን ስል ሁላቹህም በረሀ ግቡ ማለቴ አይደለም፡፡ ምናልባትም ብዙዎቻቹህ በዕድሜ የገፋቹህ ትሆኑ ይሆንና ይሄንን ማድረግ ያስቸግራቹህ ይሆናል፡፡ ሌላም ሌላም የትጥቅ ትግሉን በአካል ለመቀላቀል የማያስችሉ የጤናና የመሳሰሉ እክሎችም ይኖሩ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ባላቹህበት ቦታ ሆናቹህ እየሠራቹህ ትግሉን በገንዘብ ብትደግፉ፣ በየተሠማራቹህበት የሥራ ዘርፍና የሥራ የኃላፊነት ቦታ ወያኔ ተአማኒነት እንዲያጣና እንዲዳከም የሚያደርጉ የሚያስችሉ ሥራዎችን መሥራት ብትችሉ በግንባር ተሰልፎ ነፍሱን ለመስጠት ከቆረጠ ከተሰለፈ ከተዘጋጀ ታጋይ ያልተናነሰ ዋጋ አላቹህና በዚህ መልኩም መታገል ይቻላል፡፡

ብልጥ ሆነን ያሉ ዕድሎችን ለመጠቀም ፈተናን በብልጠት የማለፉ ብቃትና ብስለት ካለንና ዓላማችን የግል ጥቅምን ለማስጠበቅና ለሥልጣን ሽሚያ ካልሆነ ለዚህች ለምንወዳት ሀገርና ሕዝቧ ከሆነ ይሄንን ከማድረግ የሚገድበን አንዳችም እንቅፋት መሰናከል ይኖራል ብየ አላምንም፡፡ እውነት ነው ትግል ነውና ፈተናዎች ተግዳሮቶች መሰናከሎች ይኖራሉ፡፡ ይሁን እንጅ ነጻነት የሚያስፈልገው የነጻነት ጥመኛ ነን ካልን የሚጋረጡብንን ፈተና መሰናከሎች ለመሻገር ለመወጣት የሚያስችል ብልጠት ጽናት ንቃትና ዝግጅት ይዘን ያለው ዕድል ከጸጉር የቀጠነ እንኳን ቢሆን ከእግዚአብሔርን ጋር ትግሉን ለመወጣት ይቆርጣል እንጅ እጅ ሰጥቶ ለእርድ አይቀርብምና ያለ የሌለ ምክንያት መቀበጣጠር አይገባም፡፡

ገንዘብንም ነፍስንም ለመስጠት ሳንቆርጥ ወይም ከተጠቀሱት ድጋፎች አንዱንም ማድረግ ሳንችልና ሳንፈልግ ግን “ሀገሬን እወዳለሁ!” ምንትስ ብንል የምንቀልደው የምናፌዘው በራሳችን እንጅ በሌላ በማንም አይደለም፡፡ የመንግሥትንም ሥልጣን ለመያዝ ያሳሳቹህም የሚያሻማቹህም ከግል ጥቅም አሳዳጅነታቹህ፣ ዝናና ዕውቅናን ፈላጊነታቹህ እንጅ በእርግጥም የዚህች ሀገርና የሕዝቧ እጣ ፋንታ አሳስቧቹህ፣ እንቅልፍ እረፍት ነስቷቹህ አሳጥቷቹህ አይደለም፡፡

“አይ አይደለም! እኛ ለሀገራችንና ለሕዝባችን የማንከፍለው ዋጋ የለም!” ካላቹህ ደግሞ ነገ ዛሬ ሳትሉ የትጥቅ ትግሉን ተቀላቀሉ፡፡ የሥልጣን ክፍፍል አያሳስባቹህ የትግሉ ዓላማና ግብ እሱ አይደለምና፡፡ ለሥልጣን ክፍፍል ጊዜውና ቦታው ላይ ሲደረስም በፍትሐዊና ዲሞክራሲያዊ (መስፍነ ሕዝባዊ) ምርጫ ብቻ የሚፈታ በመሆኑ ይሄ ፈጽሞ ሊያስባቹህ የሚገባ ጉዳይ

አይደለም፡፡ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚያስቀድም የግል ጥቅሙ በፍጹም አያሳስበውም፡፡ ሀገር ትቅደም! ሕዝብ ይቅደም! ኢትዮጵያ ትቅደም!

ይሄ ከሆነ ምንም የሚረብሽ ነገር አይኖርም፡፡ ነገር ግን እንደደርግ ባለሥልጣናት ለሥልጣንና ለግል ጥቅም እየተሽቀዳደምን “ኢትዮጵያ ትቅደም!” ብንል መልሰን ወዳሳለፍነው ማጥ እንሰጥም እንደሆን ነው እንጅ ሀገርና ሕዝብን የሚጠቅም አንዳችም ሚና ልንጫወት የምንችልበት ዕድል አይኖርም፡፡

የትጥቅ ትግሉን የግድ አስፈላጊ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንድ ሁለቱን መጥቀስ ቢያስፈልግ፡-

አንደኛው ወያኔ “በእኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል አንተሳሰቡ” ሆን ብሎ ከፈጠረው የእርስ በእርስ ግጭት ሥጋት አኳያ የታጠቀ ኃይል መኖሩ ሕዝቡን “ዐመፅ አድርጌ ወያኔን ባስወግድ ካለበት ደርሶ ሁኔታዎችን የሚቆጣጠር፣ ይህ ችግር እንዳይፈጠር የመከላከል የማረጋጋቱን ሚና ይጫወትልኛል ከዚህ ከሚፈራው ችግርም እድናለሁ” ብሎ እንዲያምንና እንዲደፋፈር የወያኔን ማስፈራሪያ እንዲንቅ ያደርገዋል፡፡

ሁለተኛ ምናልባት በተለያየ ምክንያት ሕዝቡ ዐመፅ አድርጎ ወያኔን የመገላገሉ ዕድል ቢጠብ ወያኔ ለዘለዓለም በጫንቃው ላይ ተጭኖ የሚኖርበትን ሁኔታ “ምን አማራጭ አለኝ? ይሁንለት!” ብሎ እንዳይቀበልና “በትጥቅ ትግል ገርስሸ ሀገሬን ነጻ አወጣለሁ! በትጥቅ ትግል መምጣቱም የወያኔ ሠራዊት ሲፈርስ ሲበተን ወያኔ በሀገርና በሕዝብ ላይ የጋረጠብንን ዘርንና ሃይማኖትን መሠረት አድርጎ ሊነሣ የሚችልን የእርስ በእርስ የግጭት አደጋና ሥጋትን በሚገባ ለመከላከል ለማክሸፍ ያስችለኛ

” ብሎ እንዲያምንና እንዲያደርገውም ያስችለዋል፡፡

የታጠቀ የአንድነት ኃይል መኖሩ እስከ አሁን ተጠናክሮ የወጣ የኢትዮጵያን ሕልውና ማስጠበቅ ዓላማው ያደረገ የታጠቀ ኃይል አለመኖሩ ወያኔ እሱ ባይኖር ሊከተል የሚችለውን ቀውስ በማስፈራሪያነት እየተጠቀመ ሕዝቡን አሜን ብሎ እንዲገዛለት ለማድረግ ሲጠቀምበት እንደመኖሩ ሁሉ ይህ ኃይል መፈጠሩ ሕዝቡን ከዚህ ሥጋት ነጻ አድርጎት የሚተማመንበትን አማራጭ እንዲኖረው ያስችላል፡፡

እንዲህ ዓይነት መተማመን በሕዝቡ ልብ ሲፈጠር ብቻ ነው ሕዝብ ከታጠቀው ኃይል ጋር በመናበብ በልበ ሙሉነት ለማመፅና ወያኔን ለማስወገድ እንዲችል የሚያደርገው፡፡ የታጠቀ ኃይል መኖሩ ሕዝቡን ሁለት አማራጭ እንዲኖረው ያስችላል፡፡

የታጠቀ የአንድነት ኃይል መኖሩ ወያኔ በወደቀ ጊዜ ሠራዊቱ ሲፈርስ ከዚህ ሠራዊት የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጉዳይ የሚገዳቸውን ወገኖች ወያኔ የጋረጠብንን ሥጋቶች ከመከላከል አኳያ በተደራጀና ባልተደራጀ በቡድንም በግልም የዜግነት ግዴታቸውን በመወጣት ጠቃሚ ሚና እንዲጫወቱ ያስችላቸዋል፡፡

ባጠቃላይ የታጠቀው ኃይልና ሕዝቡ በመናበብ በመደጋገፍ መንቀሳቀስ ሲችሉ ብቻ ነው ወያኔ ወደ መቃብሩ ሊወርድ የሚችለው፡፡ የታጠቀ የአንድነት ኃይል ሳይኖር ከላይ በገለጽኳቸው መሰሪ ችግሮች ተተብትቦ ባለው ሕዝብ ብቻ ለውጥ ሊመጣ ይችላል ብላቹህ የምታስቡ ወገኖች ካላቹህ የዘመነ ወያኔ ኢትዮጵያንና ወያኔ የፈጠራቸውን ያፈጠጡ ያገጠጡ ሥጋቶችን ጨርሶ ምንም የማታውቁ ምንም ነገር ማየትና መረዳት የማትችሉ ከንቱዎች መሆናቹህን በድፍረት ልነግራቹህ እወዳለሁ፡፡

ይህች ሀገር ሽግግር ማድረግ ካለባት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ተቆጣጥሮ ይህንን ሽግግር ለማድረግ ለራሱ ቃል የገባ የታጠቀ የአንድነት ኃይል የግድ የግድ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ የታጠቀ ኃይል በሀገራችን ያለው ታሪክ መልካም ስላልሆነ የታጠቀ ኃይል ሲባል ደርግንና ወያኔን እያሰብን ሌላም ቢመጣ እንደዚያው የሚሆን እየመሰለን በመጭው እምነት መጣል የሚቸግረን ሰዎች በርካቶች አለን፡፡ ነገር ግን ዛሬ  በዓለማችን መስፍነ ሕዝብ (ዲሞክራሲ) የሰፈነባቸው ሀገራት ይሄንን ሽግግር ለማድረግ የበቁት ሽግግሩን ለማምጣት ቆርጠው በታገሉና በተሳካላቸውም የታጠቁ ኃይሎቻቸው መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

ሁለት ዕድል ከሸፈ ማለት ለዘለዓለሙ አይሳካም ማለት አይደለም፡፡ ዕድሉን አግኝቶ ያልታየን ያልተፈተሸን አካል መኮነን፣ ደምድሞ መፈረጅ፣ ማጠልሸት ከጀርባው ሌላ ዓላማ ከሌለው ጨለምተኝነትና ድንቁርና ነው፡፡ የአርበኞች ግንቦት ሰባት ኃይል የታጠቀ ኃይል ስለሆነ ብቻ "ሥልጣን ቢይዝ ከደርግና ከወያኔ የተለየ አይሆንም!" የሚሉ ሰዎች ይሄንን የሚሉት ወያኔን ዘለዓለማዊ የማድረግ ድብቅ ዓላማ ከማንገብ ካልሆነ ይሄንን የሚሉት ሌላው ቢቀር አርፈን በመቀመጥ ለወያኔ ዕድሜ ብንሰጠው ወያኔ ጊዜ አግኝቶ ጡንቻውን እንዲያፈረጥም ዕድል ሰጥተነው ያለውን ሰይጣናዊ ዓላማ ሁሉ እንዲፈጽምብንና ለባሰ አደጋ የምንዳረግ በመሆኑ ምንም አማራጭ የለምና የተገኘውን አማራጭ ሁሉ በመጠቀም የትጥቅ ትግል መደረጉን በፍጹም ሊኮንኑ ሊቃወሙ እንደማይገባ ሊገነዘቡ ይገባል፡፡

ጠለቅ ብለን እንመርምር ካልን እውነት እንነጋገር ካልን ሲጀመርም ቢሆን ደርግም ሆነ ወያኔ በተለይ ወያኔ ግልጽ በሆነ መልኩ ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ ጠባብና አደገኛ የዘር ጥላቻ የተሞላ የዘር ማጥፋት ዓላማና የጥፋት ተልእኮ አንግቦ የተነሣ የጥፋት ኃይል ስለነበር በፍጹም ለሥርዓት ሽግግር ብቁ ታማኝና የሚመጥን ተፈጥሮ ቁመና ብቃትና ሰብእና እንዳልነበረው ግልጽ ነበር፡፡ ደርግም ቢሆን "ካለኔ በስተቀር" የሚል ከፍተኛ የሥልጣን ጥማት የነበረበት ኃይል ስለነበር እሱም ምሳሌ

ሊሆን አይችልም፡፡ እናም ሁለቱም የሥርዓት ሽግግር በዚህች ሀገር ለማምጣት የሚያስችል አቅም ብቃት ታማኝነት ችሎታ እንዳልነበራቸው በሚገባ ይታወቅ ስለነበር በምንም ሁኔታ ቢሆን ለምሳሌለት የሚበቁ አይደሉም፡፡

አርበኞች ግንቦት ሰባትን ያየን እንደሆነ ግን በምንም መልኩ ብናየው አምስት እጅ እንኳን ቢሆን ከደርግና ከወያኔ ጋር ተመሳሳይነት የለውም፡፡ ወያኔና ደርግ ያደረጉትን ላድርግ ቢልም እንኳን ጊዜውም ሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎችም የሚፈቅዱለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ይህ የታጠቀ የአንድነት ኃይል ያስፈልገናል፡፡

የትም ሀገር ቢሆን ለመስፍነ ሕዝባዊ (ለዲሞክራሲያዊ) ሥርዓት ታማኝ በሆኑ የታጠቁ ኃይሎች ሳይታገዝ ወደ መስፍነ ሕዝባዊ (ዲሞክራሲያዊ) ሥርዓት የተሸጋገረ አንድም ሀገር የለም፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com